# ቅሌት ተስቦ ቶሮንቶ

'ሚሎሥ' ከቶሮንቶ፤ ካናዳ

በመከረኛው የወያኔ የሰቆቃና የግፍ ዘመን በፍርሃት ይሁን በአድርባይነት፣ በጊዜያዊ ጥቅም ይሁን በሥልጣን ጉጉት ወይም በመወናበድ፤ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከአገርና የሕዝብ ጠላት ጋር የማበር ቅሌት ውስጥ የተዘፈቁትን ስማቸውን ከታሪክ መዝገቢ እንተወውና ብዙ ናቸው። ይህ ከጳጳስ እስከ ዲያቆን፣ ከሼኩ እስከ ይማም፣ ከምሁር እስከ እስከ መሃይም እንዲሁም ጀግና ስፖርተኛውን ጨምሮ ዕውቅ የኪነት ሰዎችን ያካተተው የቅሌት ተስቦ፤ በአገራችን ከፍትህ፣ ከዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ለማስፈን በሚደረገው ትግል ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ፤ አንዱ በገዛ ፈቃዱ ወይም በወያኔ/ሻቢያ መሰሪ ተንኮል ተጠልፎ ''በቅሌት ተስቦ'' ሲለከፍ፤ ወዲያው አኮብካቢዎች መተካታቸው ነው። በዚህ በቶሮንቶም ሆነ በተለያዩ አገራት የምትኖሩ በአካባቢያችሁ የሚከናወኑትን ለአፍታ ብትታዘቡ፤ ከሌላው በዕውቀትም ሆነ በአመለካከት የተሻልን ነን በሚል ባዶ ኩፈሳና ዝና ፍለጋ ወይም በጥቂቶች ግፊትና አጨብጫቢነት ሕዝብን የመናቅ አባዜ የተፀናወታቸው ግለሰቦች ለውርደቶች ሁሉ መዘዝ መሆናቸውን ትረዳላችሁ።

ስም ሳንጠቅስ የገቡበትን የቅሌት ጉዳይ በጥቂቱ አንኳር አንኳሩን ስናነሳ፤

1. የኢትዮጵያን አንድነት በተፃረር መልኩ ሕዝብ ያልወሰነውና ያልደገፈውን አምና የተቀበለውን፣
2. ወያኔና ሻቢያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ በሃገራችንና በሕዝባችን ላይ የፈፀሙት ድርጊት በቀላሉ የሚረሳና የሚታለፍ አይደለም። ሆኖም ይህንኑ በመዘንጋት ወያኔ ያስኮረፈው ሻቢያ ኢትዮጵያን ለማዳን እንደተላከ መሲህ ተቀብለው ጫማ ሥር የወደቁትን
3. ከዚያው ተያይዞ ለስምንት ዓመታት የወያኔ ምክትል መሪ ሆኖ ሀገር ሲያፈራርስና ሲያደማ፣ ሲዘርፍ የነበረውን ታጋይ ሰየ አብረሃን እንደ ስሙ የሆሳዕና ዘንባባ ይዞ እንደተነሳ አስመስለው የሚሰብኩንን፤ የቅሌት ተስቦ የለከፋቸው እያሉ መጠቃቀስ ይቻላል።

ለዚህ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ በቶሮንቶ የቅንጅት ድጋፍ ተጠሪዎችና በወያኔ ግልገሎች መሃከል ሽምግልና ተጀምሮ ባለመሳካቱ የተበሳጩ ሽማግሌ ተብዬዎች የፃፉት ደብዳቤ፤ ተለጣፊዎቹ ያዘጋጁት በራሪ ወረቀት መናጆ ሆኖ ከቅዳሴ በህዋላ በቤተክርስቲያን ደጃፍ ሲታደል ደርሶኝ አነበብኩት። የደብዳቤው አልበቃ ብሎ ከሽማግሌዎቹ አንዱ የሆኑት የኢትዮጵያ ማህበር ባዘጋጀው የአድዋ በአል ላይ ስለ ሽምግልናው አውስተው በማህበሩ ስም በመማፀን ያደረጉት ንግግር ሙሉ ቃል በአካባቢያችን በሚታተም ''ትዝታ'' ጋዜጣ ፌብሩዋሪ 26 ቀን 2008 አ/ም ላይ ለንባብ በቅቶ ብዙኃኑን የአካባቢውን ነዋሪ በማስቆጣቱ ጉዳዩ በዝምታ መታለፍ እንደሌለበት፣ እንዲህ ዓይነቱ ''ተስቦ'' በሌላ መልኩ እየተራባ እንዳይዛመትም የበኩሌን አስተያየት ልሰነዝር ወሰንኩ።

በቶሮንቶ የኢትዮጵያ ማህበር በየዓመቱ አኩሪውን የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓልን ስለሚያዘጋጅ አድናቆቴና አክብሮቴን በዚሁ አጋጣሚ እገልፃለሁ። በዚሁ በአንድ መቶ አስራ ሁለተኛው በዓል ላይ ሁለት ነገሮች እጅጉን አስደንግጠውኛል።

1ኛው. በአድዋው በአል ላይ በኢትዮጵያ ማህበር ስም ''የኤች አይ ቪ ኤድስን'' ማስታወቂያ በመታከክ ሙያዊ ብቃትና ዲሲፕሊን በጎደላቸውና በአስተሳሰብ ድኩማን በተዘጋጀው በራሪ ወረቀት በኩል በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ማስተላለፍ የተፈለገ የስላቅ መልዕክት ነው። ይህም ''የኢትዮጵያ ጀግና'' በባህላዊ የጦር አልባሳት ተክኖ፣ በእጁ ማህደረ ብልት (ኮንዶም) በማስጨበጥና በጋሻውም ላይ ማህደረ ብልት በመለጣጠፍ የተዘጋጀውና ለሕዝብ የታደለው ማስታውቂያ፤ የሃገራችንና የሕዝባችን ክብር እንዲሁም አኩሪውን የነፃነት ዓርማና እኛነታችንን ለመፈታተን የተካሄደ የወያኔ/ሻቢያዊ ቀልድ ነበር። ድርጊቱ በኢትዮጵያ ማህበር ጥላ ስር ያውም የቀደምት የጀግኖች አባቶችና እናቶቻችንን ገድል በምንዘክርበት የአድዋ ክብረ በአል ላይ መበተኑ ያሳዝናል።

ለውድ ሃገራቸው፣ ለሰምነታቸው፣ ለሕዝባቸው፣ እግዚአብሔር በአምሳሉ ለፈጠረው የሰው ልጅ ክብርና ነፃነት ውድ ሕይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ የጀግኖቻችን መታሰቢያና የኢትዮጵያዊ አርበኛ መለያ ምስል ከትውልድ ወደ ትውልድ በክብር መተላለፍ ያለበት አኩሪ ቅርሳችን ሲሆን ልንንከባከበውና ልንጠብቀው ይገባል። በምኖርባት ካናዳ በግለሰብም ሆነ በተደራጀ መልኩ በማህበረሰብ ስነ ልቦና ላይ ሆን ተብለው የሚካሄዱ ደባዎች በህግ ሊያስጠይቁ የሚችሉ ሲሆን በዚህ አድራጎት ላይ የተሳተፉ የፖለቲካ ቁማርተኞች ማህበሩን እንደ ሽፋን በመጠቀም ከሚፈጽሙት ከእኩይ ድርጊታቸው ታቅበው ኢትዮጵያውያንን ይቅርታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

2^{ተኛው}. የማህበሩ ፕሬዚደንት ባሰሙት ንግግር የአድዋን ታሪክ በሸጋ አገላለጽ ከተናገሩ በህዋላ በመጨረሻው ላይ አነጋጋሪውን ንግግራቸው ሲደመድሙ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲሁም ሕዝብ ለዲሞክራሲ መስፈን በሚያደርገው ትግል ላይ የዘመቱትን አጥፊዎች ነፍስ ለመዝራት በአንጋፋውና በአኩሪው ማህበራችን ሥም እንደዚያ ያለ ሽምግልና ተብዬ ተማጽኖ ማቅረባቸው ነው። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ሽማግሌ ተብዬው ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ሽመገልኩ የሚሉን የኢትዮጵያን ሕዝብ ህጋዊ ወኪሎችና የወያኔን ቁንጮ ሲሆን፤ የቶሮንቶዎቹ ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ትግል ድጋፍ ሰጪ ሕጋዊ ተወካዮችና የወያኔ አሽከሮችን ሊሸመግሉ መነሳታቸው ነው።

በማንኛውም ወቅት በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ጉልህ ቅራኔዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ቅራኔዎች የሚፈጥሯቸው በጎም ሆነ መጥፎ ክስተቶችን በማስተናገድ ለማህበረሰቡ ጠቃሚውን አንጥሮ ለማውጣት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ የቅራኔዎቹን የሂደት ሰንሰለትና አፈጣጠር ከመሠረቱ ማጤን ይኖርባቸዋል። እዚያም ላይ ተመርኩዞ በግለሰቦችም ይሁን በሕብረተሰብ ወ.ዘ.ተ ላይ ሊያደርሱት የሚችለው ተፅዕኖ ከታሪካዊ ሂደታቸው ጋር ተገምግሞ በጊዜው ከተገቢው ምላሽ ጋር ይቋጫል። ይህ ካልሆነ ክስተቱ ይዛባና ተራብቶ ''<u>በተስቦነት</u>'' ይዛመታል።

ሽምግልናን በተመለከተ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ''አልቻልኩም'' በሚል ርዕሥ የፃፉት ድንቅ ጽሑፍ እጅግ አስተማሪ በመሆኑ በሽምግልና ሥም ስህተት ውስጥ የገቡ ሰዎች ደግመው እንዲመለከቱት አለፍ አለፍ እያልኩ ጽሑፋቸውን ላመልክት።

''ለሽምግልና የሚመረጠው ማን ነው? ሁለት ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቧቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። በቅንጅት አመራርና በወያኔ መሪ መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት ሽማግሌዎች ገብተውበታል ማለት በባህሉ ማሾፍ ነው። . . . ግፋ ቢል <u>አማላጆች</u> ናቸው።''

ከላይ የተጠቀሰውን የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን ገለፃ ተመርኩዞን በንፁህ ሕሊና ጉዳዩን ስናጤን፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ትክክለኛውን የኢትዮጵያ ባህላዊ ሽምግልና ፅንሰ ሃሳብ አዛብተው በመጠቀም የፈፀሙት ድርጊት የሽምግልና ሳይሆን ወያኔን በድንቁርና ከተዘፈቀበት መከራ ለማውጣት የተደረገ የምልጃ ተልዕኮ መሆኑን ግልጽና ቀላል በሆነ አባባል አስቀምጠውታል።

እስቲ ደግሞ የቶሮንቶ ሽምጋዮችን ሙከራም ሆነ በስንብት ደብዳቤያቸው ላይ የተፃፈውን አለፍ አለፍ እያልን እንመልከት። . . . '' ወደ ፍርድቤት እንደደረሰ ስለሰማን በቶሮንቶ የምንኖር ችግሩ የሁላችንም መሆኑን ተገንዝበን ካለፈው ጥቅምት ጀምሮ . . .እርስዎ የሚመሩት ድርጅት የቦርድ አባላት በተቀጠራችሁበት ቀን በግንባር መጥታችሁ የመታረቁን ሁኔታ ለመስማት ፈቃደኛ በመሆናችሁ. . . .እኛ በበጎ ፈቃድ ለዚህ ሽምግልና የተሰለፍን ሽማግሌዎች እጅግ በጣም እናመሰግናለን። (*ይህ ምስጋና የተዥጎደጎደው ለተለጣፊዎቹ፣ ለሌባ አይነደረቆቹ ነው*)
ይቀጥሉና .....የጀመርነውና የደከምንበት ሁሉ ያለውጤት በመቅረቱ እያዘንን...ሁለታችሁንም ወገን የሚያስማማው ሃያሉ እግዚአብሔር ስለሆነ እርሱ በሚመራችሁ እርቀ ሰላም እንድታወርዱ እየተመኘን . . . '' የአራት ሽማግሌዎች ፊርማ ያለበት።

በዚህ በቶሮንቶ የተፈጠረው ጉዳይ የፕሮፌሰር ኤፍሬምን የካርቦን ቅጅ ይመስላል፤ የጫወታ ሜዳውና ሕጉ ሌላ ሆነ እንጂ። የኛዎቹ ሽማግሌ ነን ባዮች ከአገሩ ርቆ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊና እዚህ አገር የተወለዱትን ጭምር ስለ ''ኢትዮጵያ የሽምግልና ባህል'' የተዛባና አደናጋሪ ትንታኔ በመስጠት አይን ጨፍኑ ላሞኛችሁ ሲሉን፤ የለም ተሳስታችኋል፣ ባህላችን ሳይበረዝ ሳይከለስ ለመጪው ትውልድ ይተላለፋል ''<u>ምልጃን ከሽምግልና</u>'' ጋር አታምታቱ ለማለት መድፈር ይኖርብናል።

ለዚህ ደብዳቤ አስተያየቴን ከመስጠቴ በፊት ስለ ሽምግልና ትንሽ ጠቀስ አድርጌ ልለፍ ። ለሽምግልና የሚመረጡ ዳኛም ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ እውነትን የሚመረኮዙ ሃቀኛ ሚዛን የሚይዙ አስተዋይ፤ በታረመ ጠንቃቃ ቃል ይሸመግላሉ ስለሚባል ውጤታቸው ያማረና የሠመረ ሆኖ እርቀ ሠላም ያወርዳሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው።

ለጉዳዩ ቀረቤታ ላለው ለማስታወስ ለራቀውም ለማሳወቅ በቅድሚያ የአንጃ ግራንጃውንና የክሱን መነሻ ላንሳ። የቅንጅት ስያሜና መለያ፤ የሕዝብ ሃብት መሆኑን አንድ ጊዜ አይደለም ብዙ ጊዜ በመደጋገም መፈክሩን ሰምቻለሁ። እኔም እጋራዋለሁ። ነገር ግን በዚህ በካናዳ ፍትህና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት አገር በመኖራችን ቀደም ሲል በቅንጅት የኢትዮጵያ የባህልና የዕርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ቡድን የቅንጅት መለያ ሕጋዊ ተወካይ ሆኖ ድርጅቱንም በሕግ አስመዝግቦ ለሃገርና ለወገን የአቅሙን ያህል እየሰራ መሆኑ በይፋ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ማፍረስና መከፋፈል ልዩ መለያው የሆነው ወያኔ ባህር ተሻግሮ ተለጣፊ ምስለኔዎቹን በማንቀሳቀስ ቅንጅትን በካናዳ ምድር ግብግብ ገጠመ። ወያኔ የሕዝብ ወገንና የአንድነት ኃይል የሆኑ ድርጅቶችን ለማጥፋት የሚጠቀመው ''ባረጀና ባፈጀ ስልቱ ተለጣፊ በማቋቋም ህዝብ ግራ እንዲጋባ፣ በድርጅቶች ላይ እምነት እንዳይኖረውና አገር ቤት ለሚደረገው ትግል በሞራልም ሆነ በገንዘብ የሚደረገው ድጋፍ እንዲዳከም ነውና'' ይህንኑ ለመተግበር በቶሮንቶ የፀረ አንድነት

ፍልሚያውን በራሱ ዳኞች ሊቆጣጠረውና እንደፈለገው ሊያዝ በማይችልበት አገር በእነ አንዳርጋቸው ፅጌና ብርሃኑ ነጋ ካድሬዎች ላይ ዕምነቱን ጥሎ የካናዳን ሕግና ሥርዓትን ጣሰ። የዚያ የቅን ሕዝባችን አምላክ የአዞ እንባ አንቢ የወያኔ ግልገሎችና ባንዳዎችን በዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች እጅ ጣላቸው። የአንድነት ኃይሉም በሚቆጣጠረው ቀጠና የሚኖርበትን አገር ህግና ሥርዓትን ተከትሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላምና ዲሞክራሲ ትግል እንዲሁም በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ህልውና ላይ ያነጣጠረውን አደጋ ከመመከት በቆራጥነት ተነሳ።

የቶሮንቶው ቅንጅት ቀድሞውኑ የቅንጅትን ስምና አርማ በካናዳ ሕግና ደንብ አስመዝግቦ ይንቀሳቀስ ስለነበር፤ ሌላ ተከጣፊ በወያኔ አይዞህ ባይነት ስሙንና አርማውን ተጋርቶ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ሲሳለቅ በማን አለብኝነት የካናዳን ሕግ ሲጥስ ዝም ብሎ የሚያይበት ምክንያት አይኖርም። ሥርአተ አልበኞችና ግብረ አበሮቻቸው ለሚሰሩት ድርጊት በሕግ ፊት ተጠያቂ ሰለመሆናቸው እስኪገባቸው ማስተማር ያስፈልጋል። ማንም እየተነሳ በሕዝብ ግፍና ሥቃይ ሥም ሲነግድ፤ መቀጣጫ እንዲሆንና ሌሎችም ድንቁርናና ትብዒትን በላያቸው አንግሰው በውጭው አለም በሚኖረው ኢትዮጵያዊ ተቋማት ላይ በተለያየ የጥፋት መንገድ የሚዘምቱትን ለማስተማር የተወሰደውን የክስ እርምጃ ብዙሃኖች ደጋፊ ነን። ነገር ግን በተከበረ ዕውነተኛ ሽምግልና ወይም ከፈጣሪ ክልብ የተገዘ፤..... *መስሎን አሳስተውን ነው። ለሠራነው ሥሕተት ሁሉ በይፋ ሕዝብ በተሰበሰበበት ይቅርታ እንጠይቃለን።* ከሆነ ብቻ ነው እርቁ በባህላችን ተቀባይነት የሚኖረው።

አዎ ከዚህን ቀደም ታላቁን የቶሮንቶን መረዳጃ ዕድር ለማፍረስ ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ በዚሁ በተለጣፊው ቡድን ውስጥ መሽገው ወደ ኢትዮጵያ ማህበር ኮቴያቸውን በማስገባት ማህበሩን አላላውስ ብለው ለአንድ አመት እንደ ወጋት ቀስፈው በመያዝ ምንም ሥራ አለመሠራቱን ''እሁድ አፕሪል 13 ቀን 2008 አ/ም '' በማህበሩ አመታዊ ጉባኤ ላይ ከተካሄደው ግምገማ መረዳት ተችሏል። በዕለቱም ግርግር በመፍጠር ፕሬዚደንቱን (ከሽማግሌዎቹ አንዱ የሆኑትን) ከኃላፊነት ለማንሳት በተበላው የወያኔ ስልት ተንደፋድፈው ነበር። ሆኖም ማህበሩን እንደ አይናቸው ብሌን የሚጠብቁ ኢትዮጵያውያን አሳፍረው መልሰዋቸዋል።

ወያኔ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝብዋ በቆሙት፤ በመምህራን ማህበር፣ በሠራተኛ ማህበር፣ በነፃው ፕሬስ፣ በወጣት ማህበር፣ በሴቶች ማህበር፣ በኃይማኖትና በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የራሱን እኩይ ዓላማ የሚያራምዱ ተለጣፊዎችን አገር ቤት በሾማቸው ካድሬ ዳኞቹ አማካይነት ውሳኔ እያሰጠ በማቋቋም የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማጭበርበር የተጠቀምበትን ኋላቀር ስልት የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበርና አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ምን ያህል በቆራጥነት ታግለው የወያኔ/ኢህአዴግን አገዛዝ በምዕራባውያን አሳዳሪዎቹ ፊት ዕርቃኑን እንዳቆሙት ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም። ታዲያ የኛዎቹ ሽማግሌዎች የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ የሆኑትን መክረውና ተቆጥተው ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ጫና ከመፍጠር፣ ያስቀየሙትን ወገናቸውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ከማድረግ ይልቅ በምስጋና ደብዳቤ ተለጣፊዎችን በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ላይ ''ጃስ'' ማለታቸው ብዙኃኑን እንዳስቆጣ ሊረዱት ይገባል።

በቶሮንቶ በበጎ ፈቃድ ተነሳን የሚሉት ሽማግሌዎች (*ነገሩ የአደባባይ ሚስጢር ነው። ሰፊው ሕዝብ እንደተረዳው በየድርጅቱ በተሰገሰጉ አድርባዮች ጉትጎታና ምልጃ እንዲሁም እነ ብርቱካን ከወያኔ ጋር ስምምነት ፈጥረው የምዕራቡን ቅባ ቅዱስ ታብሰው ሊነግሡ እንደሆነ.. ወሬው ስለተናፈሰ ልክ እንደ ቡሄ ዋዜማ ጅራፍ እኛም አለን ለማለት ካልሆነ በቀር የሽምግልናን መስፈርት አያሟላም*...) ይህ ህጋዊ ክስ ግልጽ እንደሆነ ማንም ይረዳዋል። ታዲያ እንዴት ነው ''.... ፍርድ ቤት እንደደረሰ ስለ ሰማን በቶሮንቶ የምንኖር ችግሩ የሁላችንም መሆኑን ተገንዝበን...'' የሚለው? አቤት ግንዛቤ! ቶሮንቶ የወያኔ ምሽግ የለም። ችግሩ የጥቂቶች እንጂ ሽማግሌዎቹ በደብዳቤው ላይ እንደጠቀሳችሁት የሁላችን አይደለም።

ከዚያም.. ''የመታረቁን ሁኔታ ለመስማት'' ይላሉ ሽማግሌዎቹ። የእነ ማንን ዜና ለመስማት ነው የመጡት? ''.. በበጎ ፈቃድ ለዚህ ሽምግልና የተሰለፍን...'' ይላል ደግሞ ወረድ ብሎ፤ በየትኛው ኢትዮጵያዊ ባህል ሽማግሌ በበጎ ፈቃድ ሽማግሌ ሆኖ የሚቀርበው? በባህላችን ሽማግሌ ክቡር ነው። የሽምግልና ወግና ማዕረጉ የሚደርሳቸው የዕድሜ ባለፀጎች፣ ከኑሮና ከሕይወት ተምረው ልምድን ያካበቱ፣ በሚሰጡት አስተያየትም ሆነ ዳኝነት ወገንተኝነት የማያጠቃቸው፣ በአርቆ አስተዋይነታቸውና በሚያፈልቁት ሃሳብ፣ አስተያየትና ምክር የሚከበሩና የሚደመጡ ናቸው።

''... ለዚህ ሽምግልና የተሰለፍን ሽማግሌዎች እጅግ በጣም እናመሰግናለን..'' ይላል። ምስጋና? እንዴትና ማንን? በግልባጭ ምስጋናው ''ኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ አላት፣ ጥቂት አማሮች ጠፍጥፈው የፈጠሯት ነው...'' ብሎ ለተሳለቀብን ባንዳ በመድረሱ፤ ብርሃኑ ነጋ ከሙታን መሃል ተስቦ ቶሮንቶን ሊረግጥ ተዳፈረ። ተለጣፊዎቹ በሽምግልና ካባ ምን ያህል ለፀረ አንድነት ኃይሎችና የባዕዳንን ተልዕኮ ለሚፈጽሙ ቅጥረኞች እንደሠሩና ሽማግሌዎቹ በሕብረተሰቡ ዘንድ በጎሪጥ እንዲታዩና ለሰላ ሂስ እንዲዳረጉ እንዳመቻቹ በገሃድ ታይቷል።

ፈሪሃ እግዚአብሔር አድሮበት ሃቅና ፍትህን ተመርኩዞ የሕዝብና የወገንን ስቃይ እታደጋለሁ ብሎ የተነሳ ሽማግሌ በየትኛውም መመዘኛ ይህንን አደናጋሪ ድርጅት ተብዬ ማመስገኑ እጅግ አሳፋሪ ነው። ከጅምሩ አጉል ነበርና ደከምንበት

የተባለው ሽምግልና መና መቅረቱ ደካማነቱን አጋላጭ ነው። ደብዳቤው ከላይ አሳዝኖኝ መደምደሚያው ላይ፤ ''. . . ሁለታችሁን የሚያስማማው ኃያሉ እግዚአብሔር . . .'' የሚለውን ቃል በማየቴ ተጽናናሁ። በሽማግሌዎቹ ደብዳቤ ላይ እንደተጠቀሰው መጀመርያ ራሳቸውን መርጠው በመጨረሻ ራሳቸውን የሻሩ በመሆኑ ጉዳዩን ያነሳሁት፤ ነግ ባለ ሣምንት ብሎ ሌላው ''<u>በቅሌት ተስቦ</u>'' እንዳይያዝ ነው።

በዚህ በቶሮንቶ የተከበሩ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ወደ ካናዳ እንዲመጡ የተደረገው ጥረት ባለመሳካቱ እሳቸው ራሳቸው የፃፉትን ደብዳቤና የአደራ ጥሪ የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን በአዳራሽ ውስጥ ተገኝተው በሙሉ ልብና ቀና መንፈስ በመከታተል ዕውነታውን የተገነዘቡት ሲሆን፤ ከሽማግሌ ተብዬዎቹ አንደኛው በፍፁም ያልተገኑ፣ ሁለቱ ለይስሙላ ተገኝተው ሳይጨርሱ የወጡ ሲሆን አንደኛው በሚገባ ተከታትለው ማጠናቀቃቸውን ብዙዎች ታዝበዋል።

የሽማግሌዎቹና የጥቂት አይዞ ባዮቻቸው የመጨረሻው የፈተና ውጤት ቅዳሜ አፕሪል 19 ቀን 2008 አ/ም ይለያል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለወያኔና ለባዕዳን አሳልፎ የሰጠ ከሃዲና ባንዳውን ''ብርሃኑ ነጋን'' ሄደው እጅ ይነሳሉ ወይስ የተለጣፊዎቹ መሰሪ ተንኮል ገብቷቸው ከአንድነት ኃይሉ ጋር ይሰለፋሉ? ይህ ሰሞኑን የሚታይና ለታሪክ የሚተው ነው።

የዚህ ጽሑፍ መልዕክት፤ የከተማችንን የአደባባይ ሚስጢር ከይሉኝታ ቆፈን ፈልቅቆ በማውጣት የዕውነተኛ ኢትዮጵያውያን ስሜት ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባና ያልተረዱት በግልጽ እንዲገነዘቡት ለማድረግ ሲሆን፤ ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ በወያኔ/ሻቢያና ቡችሎቻቸው የተንኮል ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ ለማሳሰብና ወገን ለወያኔ ድንጋይ አቀባይ መሆኑ ቀርቶ ለሕዝብና ለሃገር መከታነቱን ሳያወላውል በተግባር እንዲያሳይ ለመጠቆም ነው።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ።